አፍሪካ ቲቪ

ከታላቁ ቁርአን
የመጨረሻዎቹ
‹‹የሶስቱ ክፍሎች››
ማብራሪያ
ዋና ዋቢ
ዙብደቱ ተፍሲር

# አፍሪካ አካዳሚ
# AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

7

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአቂዳ ትምህርት

በቴሌግራም

2

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

ሁለተኛው አለም አቀፍ የርቀት ትምህርት መሪ ቃል
“ትክክለኛው ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው”

إِنَّ الدِّينَ عِندَ اللَّهِ الْإِسْلَامُ

“አላህ ዘንድ የተወደደው ሀይማኖት ኢስላም ብቻ ነው ፡፡”

ሁሉንም ሙስሊም የሚመለከቱ
የአፍሪካ አካዳሚ
የርቀት ትምህርት
1441 ሒጅሪያ/2020

- **በመጨረሻ ቀን (የውመል ዓኪር) ማመን ማለት ምን ማለት ነው?**

**(የሰው ልጅ 3 ዓለሞች አሉት 1ኛ-ዱንያዊ ዓለም 2-ከሞት እስከ መቀስቀስ 3-ከመቀስቀስ ቡኋላ)**
የመጨረሻው ቀን የማይቀር መሆኑን ማመን ሲሆን በዚሁም ውስጥ የሚጠቃለሉትን ማለትም ሞትና ከዚያም ቀጥለው የሚመጡን የቀብር ፈተና (ቅጣት) እና ድሎቱ በቀንድ መነፋት፤ ሰዎች በጌታቸው ፊት ለጥያቄ መቆማቸው፤ የመዝገቦች መበተን፤ ሚዛን መቀመጡ፤ሲራጥ መኖሩ፤ ሀውድና ሸፊዐህ መኖራቸውንም ከዚያም የሰዎች መጨረሻ ወደ ጀነት ወይም ወደ እሳት መሆኑን አምኖ መቀበል ማለት ነው፡፡

## የትንሳኤ ቀን ርዝመት:

የትንሳኤ ቀን ርዝመት 50,000 (ሐምሳ ሺህ) ዓመት ያለው ሲሆን ለአማኞች ግን ከዙህር ሶላት እስከ ዐስር ሶላት ያለው ጊዜ ያህል ብቻ ነው የሚረዝምባቸው፡፡

ቁርኣን እንዲህ ይላል፡- ‘’ፊቶቹ በዚህ ቀን አብሪዎች ናቸው ሳቂዎችም ተደሳቾችም ናቸው ፊቶችም በዚያን ቀን በላያቸው ላይ ትቢያ አላቸው፡፡ ጥቁረት ትሸፍናቸዋች፡፡ እነዚያ እነሱ ከሐዲዎች አመፀኞች ናቸው’’ (ዐበሰ ቁ. 38-42)

አንዳለው ሁሉ ሙስሊሞች በደስታ ፈንድቀው አንገታቸውን ቀና አድርገው ሲውሉ ከሃዲዎች ተጨንቀውና አንገታቸውን ደፍተው ይውላሉ፡፡

**የትንሳኤ (ቂያማ)ቀን ስሞች በቁርአንና በሐዲስ ብዙ ናቸው፡፡**

**ይህ ቀን የዚህኛው ዓለም ማብቂያና የሁለተኛው ዓለም መጀመሪያው ቀን ሲሆን በቁርኣን ብዙ ስሞች አሉት፡፡**

1- ጣመቱል ኩብራ፤
2- የባዕስ ቀን፤
3-የመውጫ ቀን፤
4-የመቆሚያ ቀን፤
5-የምንዳ ቀን፤
6-የመወሰኛዋ ቀን፤
7-የመሰብሰቢያ ቀን፤
8-የሂሳብ ቀን፤
9-የዛቻ ቀን፤
10-የፀፀት ቀን፤
11-የዘላለሟ ቀን፤
12-ሌላይቷ ሀገር፤
13-የመደላደያው ቀን፤
14-የአሸናፊ ቀን፤
15-የአስደንጋጭ ቀን፤
16-የምልጃዋ ቀን፤
17-መጠራጠሪያዋ ቀን፤
18-ታላቅ ቀን ፤
19-የፍትህ ቀን፤
20-የትንሳኤ ቀን የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

## በመጨረሻ ቀን ማመን ስር የሚጠቃለሉ ነገሮች:-

የመጨረሻው ቀን የማይቀር መሆኑን ማመን ሲሆን በዚሁም ውስጥ የሚጠቃለሉትን ማለትም

1-ሞት፤

2-ከዚያም ቀጥለው የሚመጡትን የቀብር ፈተና (ቅጣት እና ድሎት)፤

- **ሶስቱ የቀብር ጥያቄዎች:-**
- (I)-ጌታህ ማነው?  (II)-ነብይህ ማነው?  (III)-ሐይማኖትህ ምንድነው?

3-በቀንድ መንፋት፤ 4-ሰዎች በጌታቸው ፊት ለጥያቄ መቆማቸው፤ 5-የመዝገቦች መበተን፤ 6-ሚዛን መቀመጡ፤

7-ሲራጥ መኖሩ፤ 8-ሀውድና ሸፋዐህ መኖራቸውንና ከዚያም የሰዎች መጨረሻ ወደ ጀነት ወይም ወደ እሳት መሆኑን አምኖ መቀበል ማለት ነው፡፡

ይህም ማለት የሰው ልጆች በሙሉ በምድራዊ ህይወታቸው ቆይታ ወቅት የሰሩትን ሥራ ዉጤት በሙሉ የሚመለከቱበትና በሰሩትም ኸይር ከሆነ በጀነት የሚመነዱበት ወይም መጥፎ በገሀነም የሚቀጡበት ቀን መኖሩን ማመን ነው፡፡

የሰው ልጆች በሚሞቱበት ጊዜ መልአከ እንደሚመጣና ላደለው በቀጥታና በእዝነት ለሻበት ደግሞ በኃይልና በጉልበት ሩሁን (ነፍሱን) እንደሚመዛት ማመን እና ከዚያም ‹መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! ፊተኞቹም ሆኑ ኋለኞቹ በተወሰነ ቀን ቀጠሮ በእርግጥ ተሰብሳቢዎች ናቸው በላቸው› (በአል-ዋቂዐህ ሱራህ ከ 49 እስከ 50)

በሚለው አንቀፅ የተነገረዉን ማመን፤

የቀብር ቅጣት ወይም ደስታ እንዳለ ማመንና ይኸውም ሩህና አካል በአንድነት ሆነው እንደሚሆን ማመን፤

- የመዝገቦች መበተን፤ ከዚም መዝገቦች ይበተናሉ፡፡

ሰዎች መፅሐፋቸውንም ይቀበላሉ፡፡ አማኙ በቀኝ እጁ ከሃዲውንና ሙናፊቁ ደግሞ ከበስተጀርባው በግራ እጁ ይሰጠዋል፡፡

- ስለ ሚዛን:- ከዚያም ምንዳቸውን እንዲያገኙ በእውነተኛና አስተማማኝ በሆነ ሁለት ሳህን ባለው ሚዛን የሰዎች ተግባር ይመዘናል፡፡

ለአላህ ንፁህ የሆነና ሸሪዓውን ገጥሞ የተፈፀመ ተግባር ሁሉ ሚዛኑን ያከብደዋል፡፡

ለምሳሌ ላኢላሀ ኢለሏህ ማለት፤ መልካም ስነ ምግባር፤ አልሐምዱሊለህ፤ ሱብሃነላህ ወቢሐምዲህ፤ ሱብሓነላህ አል ዐዚም የሚለውን ዚክር ይመስል፡፡ ሰዎች በመልካም ተግባራቸው ሆነ በመጥፎ ይመነዳሉ፡፡

ሁሉንም ሙስሊም የሚመለከቱ ስለ መጨረሻው ቀን ማመን ማለት ከሞቱ በኋላ በሚኖሩት ክስተት ውስጥ በቀብር ውስጥ ከሚከሰቱት፡-

1-ቅጣት፣

2-ደስታ፣

3-ሂሳብ፣

4-ሚዛን፣

5-ምንዳ፣

6-እሳት፣

7-ገነት፣ እና እነሱን በመሰሉት ማመን ማለት ነው፡፡ በመጨረሻው ቀን ማመን ትክክለኛ አዕምሮ ያለው ሰው ሁሉ አሚን ብሎ የሚቀበለው ሐቅ ነው፡፡

በመጨረሻ ቀን ማመን ከሚያጠቃልላቸው ዋና ዋና ነገሮች መካከል የዓለም ፍጻሜ ከመድረሱ በፊት ብዙ አንጋፋና ጥቃቅን ምልክቶች አሉ ብሎ ማመን የመጀመሪያው ሲሆን እነዚህ ምልክቶችም ሶስት ክፍሎች አሏቸው፡፡

1-ያለፉ፤

2-አሁን የሚታዩ፤ -

3-ለወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ናቸው፡፡

## የቂያማ ታላላቅ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ቂያማ ከፊት ለፊቷ አስር ታላላቅ ነገሮችን ሳታዩ አትከሰትም፡፡ ከነዚህም ጭስን፤ ደጃልን፤ ላሟን፣ ፀሐይ በምዕራብ መውጧቷን፤ የመርየም ልጅ ነብዩ የዒሳ መውረድን፤ የዕጁጅና መዕጁጅን መውጣት፤ ሶስት የመሬት ስምጠትን፤ ማለትም አንዱ በምስራቅ፤ አንዱ በምዕራብና አንዱ ደግሞ በዐረቡ ደሴት የሚከሰቱትን የመሬት ስምጠቶች የመጨረሻው ከየመን ተነስታ ሰዎችን ወደ መስብሰቢያቸው የምትነዳውን እሳት) ጠቅሰዋል፡፡

## ሀ. ያለፉት ምልክቶች፡-

1- የነብዩ ሙሐመድ ﷺ መምጣት (መላክ)፣

2-በይተል መቅዲስ በሙስሊሞች እጅ መግባት፣

3-ዑስማን ብን አፋን የተባሉት ሶስተኛው ከሊፋ መገደል፣

4-በሙስሊሞች መካከል ተከስተው የነበሩ ጦርነቶች፣

5-ከሰላሳ የማያንሱ ሀሰተኛ ነብይ ነኝ ባዮች መነሳት፣

6-የገንዘብ መብዛት፣ የመሬት ነውጥና ስምጠት መበራከትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## በአሁኑ ወቅት የሚታዩ ምልክቶች:-

1- እነርሱም ደካሞች ነግሰው ንጉሳን ረክሰው መታየት፣

2-በእምነት ላይ መፅናት እሳትን እንደመጨበጥ ሲከብድ ማየት፣

3-ሰዎች በመስጂድ ግንባት መፎካከር፣

4-የመሃይማን ፅድቅና የአዋቂዎች ማመፅ፣

5-የእውቀት ማነስና መሀይምነት መስፋፋት፣

6-የዝሙት መስፋፋት፣

7-የአስካሪ መጠጥ መንሰራፋት፣

8-የወንድ ቁጥር መቀነስ፣ የሴቶች ቁጥር መበራከት፣

9-የአማና መጥፋትና የመሳሰሉት አሁን እየታዩ ያሉ የቂያማ መከሰት ምልክቶች ናቸው፡፡

## ለወደፊት የሚመጡ ምልክቶች:-

እነሱም ግዙፍ ምልክቶች በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነርሱም:- ‹‹የትንሳኤ ቀን ሲቃረብ ብዙ እንግዳ ክስተቶች ይከሰታሉ፡፡

1-ያልታወቁና አስደናቂ ፍጡራን ይታያሉ፡፡

2-ሥነ ምግባሮች ፈር ይለቃሉ›› አሕመድ እና አቡ ኑዐይም

3-‹ለእግራቸው ጫማ የሌላቸው የፍየል እረኞች ሰማይ ጠቀስ ፎቅ መገንባት መቻላቸው ለትንሳኤ ቀን መቃረብ አንዱ ምልክት ነው› ብለዋል፡፡

4-በዘመናችን የቤትን ግድግዳ እንደ ልብስ ለመለካትና ለማስጌጥ ስዎች ወጪ ሲያወጡ ማየት የተለመደ ሆኗል፡፡ አሁን ጊዜው መጥቶ የተለመደ ይሁን እንጂ ድሮ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ስለዚህ ጉዳይ ሲናገሩ ማመኑ ከፍተኛ ኢማን ይጠይቅ ነበረ፡፡

5-“የመሬት ክፍሎች ግዛት እንድ ሆነው በፀሐዩ መውጫ ታየኝ፡፡ እናም የተከታዬቼ ግዛት በተጠቃለለኝ መሬት ስፋት ልክ ሳይሆን አይቀርም፡፡

6-የጊዜ መቀራረብ ማለትም ጊዜው በረካ አጥቶ መቅረት፣

7-ዓመት እንደ አንድ ወር፣

8-ወሩ እንደ ሳምንት፣

9-ሳምንቱ እንደ ሰዓት የሚሆንበት ማለት ነው፡፡

10-የዱር እንስሳት፣ እፅዋትና የሌሎች ፍጥረታት መናገር